# የቴዲ ነገር!

## (ለህሊና እሥረኛው - ድምጻዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን - «ቴዲ አፍሮ»)





የገዘፈውን ጨለማ - ብርሃን ቢፈነጥቅበት፣
የተዳከመውን ኢትዮጵያዊነት - እስትንፋስ ቢዘራበት፣
ፍቅር፣ ሰላም፣.. እርቅን - ዘምሮ ቢያስዘምረን፣
ለትውልዱ ራዕይ ኪዳን - ድምጹ ተስፋ ቢሆነን፤
ዘረኝነት የተጠናወታቸው - ለጥፋት ያደገደጉ፣
በእኩይ ምግባር ታንጸው - ህሊና-አልባ ያደጉ፣
በክፋት፣ በቂም፣.. በተንኮል - የታጀሉ ጨለምተኞች፣
ጥበብን አሰሩት አሉ - የድንቁርና «ሊቆች»።



ባገር ፍቅር ክትባት - ተኮትኩቶ ያደገ፣
የሕዝብ ወዳጅ ዐይነ-ግቡ - ባለ-ግርማ የደመቀ፣
ብቅ ሲል ላገር አድባር - የአንድነቱ ሰባኪ፣
በቅኔው አዋጅ ነጋሪ - በቅዱስ ዜማው ባራኪ፤
የለመለመ ቁጥቋጦ - ያማረ አበባ ሊቀጥፉ፣
ዛሬም እንደ ትናንቱ - የዕውቀትን ብርሃን ሊያጠፉ፣
ረጃጅም ጥፍሮቻቸውን አሹለው - ሟርተኞች ተነሱ አሉ፣
የጥበብን የዐይን ብሌን - በክፋት ሊደነቁሉ።






«ኤሎሄ».. እያለ ለእማማ ኢትዮጵያ ሲያለቅስላት፣
«አንበሳ».. እያለ ጀግኖቿን ሲያወድስላት፣
ሙስሊም ክርስቲያኑን እሚያስማማ፣
ሲያዜም ያብሮ መኖር ህልው ዜማ፣
ያዲስ ዘመን ተስፋን ብሥራት - እሱ ሲያይ አርቆ፣
በ«ሆ! በል ከራር፣ ሆ! በል መሰንቆ፣ ስታይ ሰው ታርቆ»..፣
አልሰማንም አሉ ጆሮ ደፍነው፣ አላየንም አሉ ተጨፍነው፣
የተናቁ!! ጥበብ ንቀው።






የጥበብ ሰው መሰረቱ፣ ፅናቱ ነው እምነቱ፤
አትበጠስም ማተቡ - የተቋጠረባት እውነቱ፤
ኃያል እንጂ ነው ብርቱ፣ የኪነ-ጥበብ ጉልበቱ፣
ላለም ሥልጣኔ ቤዛ - ለሰብዕ መድኅንነቱ፤
የሰለለ ቢመስልም በድንቁርና ባህል፣
ብረት-ሰንሰለት በጣጥሶ - አሳሪዎቹንም ነጻ ያወጣል!

ጌታቸው አበራ
ጵዋግሜ ፫ ቀን ፳፻
ሰፕቴምበር 2008

(ለተወዳጁ ድምጻዊ ቴዲ - ብርታትን፣ ጽናትንና መልካም አዲስ ዓመትን እንመኛለን!)